# በይሉኝታ አገር ሲፈርስ ቁጭ ብሎ መመልከት ከተባባሪነት የተለየ አይሆንም

ከአይምሮ ዳኛቸው

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ከባህላችን ጋር በምንም አይነት መልኩ ያልተያያዘ የማያስነውረውን እንደ ነውር ፤ አስነዋሪውን እንደ መልካም ባህል አድርገን እንድንቀበል የዘመናችን ብልጣ ብልጦች እየተጠቀሙበት ወይንም እየተጠቀሙብን ይስተዋላል ። ሳይወክሉ ተወክለናል ፤ ሳይመረጡ ተመርጠናል በማለት ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን የጎጠኞቹን አገዛዝ በምናደርገው የሞትና የሽርት ግብ ግብ ውስጥ ጣልቃ እየገቡ ትግላችንን ከቀን ወደ ቀን ወደፊት ከማራመድ ይልቅ የኋሊት እንድንሄድ ሲያደርጉን የግለሰቦቹን ማንነትና አላማቸውን ድፍረቱ ያላቸው በሚጠይቁበትና በሚያጋልጡበት ጊዜ ማንነታቸውንና ምንነታቸውን ለመሸፈን ማንነታቸውን የሚጠይቁ ጥያቂዎች ሲነሱ ከባህልና ካገር ልማድ ውጪ እንደወጡ ነውረኞች እንደሆኑ ተደርጎ ይነገራል ። ማንነታቸውን የጠየቁም ይወገዛሉ ፤ ይገለላሉ ። የግለሰቦችን ማንነትና ምን ሲሰሩ እንደነበሩ በመጠየቃቸው ብቻ ጸረ ሕብረት ፤ ጸረ አንድነት አድርገው ለማቅረብ ሲሞክሩ ይታያል ፡፡

በታሪካችን አንድ ሰው በራሱ አነሳሽነት መጥቶ እራሱን በላያችን ላይ ሲሾም አንተ ማነህ ፤ ከየት መጣህ ፤ ምን ስትሰራ ነበር ብሎ የመጠየቁ ልምዱ ስለሌለን ሁሌም እራሱን በላያችን ላይ የሾመውን ሁሉ ተቀባይ በመሆናችን ስቃዩ ወደማያባራ ዘመኑ ተቆጥሮ ወደማያልቅ ስቃይ እየተነዳን እንገኛለን ። ካለፈው የቅርቡ ታሪካችን እንኳን ብንመለከት ኮሎኔል መንግሥቱና ግብረ አበሮቹ እራሳቸውን በራሳቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሲሾሙ እናንተ እነማናችሁ ብሎ የጠየቀ ባለመኖሩ ለ17 ዓመት ያክል በግፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲጨፈጨፍ ሆኗል ፤ የወታደራዊው መንግሥትም ካለፈም በኋላ የመጣው የጎጠኞች አገዛዝ እንደዚሁ አንተ ማን ነህ? ማን ወከለህ ያለውና የጠየቀው ባለመኖሩ ይኸው ከተለመደው የግፍ አገዛዝ ወደከፋው የግፍ አገዛዝ ተሸጋግረን ዛሬም የደም እንባ እያለቀስን እንገኛለን ።

እንግዲህ ካለፈው ተሞክሯችን ሳንማር በመቅረታችን ዛሬም ግለሰቦችና ቡድኖች እራሳቸውን በራሳቸው በላያችን ላይ ሾመው እንመራችኋለን ሲሉን እንተ ማን ነህ ? ከየት መጣህ? ምን ትሰራ ነበር ብለን የጠየቅን ሁሉ የትግሉ እንቅፋት እንደሆንን ተደርጎ በየሚዲያውና ድረገጹ ሲቦካ ሲዘከር ይውላል ። ታዲያ ካለፈው ስህተታችን ያልተማርን እንዴት አድርገን ነው የወደፊቷን ኢትዮጵያ በተሻለ ልንገነባና ለሕዝቧም ነፃነት ልናጎናጽፍ የምንችለው? ለምን የግለሰቦች ማንነትና ምንነት መጠየቅ እንደ ወንጀል ወይንም እንደ ነውር ተቆጥሮ የሚራገበው? ወይንስ ጠያቂውን በማዋከብና ሥም በመስጠት እንዳለፉት ገዢዎቻችን አለጠያቂና ማነህ ባይ በስልጣን ላይ ተፈናጥጦ የማያባራውን አፈናና ጭፍጨፋ ለማካሄድ ታልሞ ነው ፡፡ እንዴት ተምረናል አውቀናል እያልን ያላዋቂ ተግባር እናራምዳለን?

ታጋይ ነን ፤ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝቧ ነፃነት የሚቻለንን እናደርጋለን ፤ ደማችንንም ቢሆን ለማፍሰስ ዝግጁ ነን እንላለን ። ይህ አባባል በእውነት ይውጋሽ ብሎ ይማርሽ ማለት አይሆንብንም? በእውነት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ይህንን ያክል የምንገበገብና የምንቆረቆር ከሆነ ታዲያ ኢትይጵያን ለማፍረስና ለመገነጣጠል ምለው የተሰለፉ ጠላቶቿን ይዘን በመዝመት ነው ኢትዮጵያን የምንታደጋትና ነፃ የምናወጣት? ወይስ አለማወቅ ይሆን? አለማወቅ ነው እንዳይባል ከማንም በላይ ተምረናል ፤ አውቀናል እያሉ የሚመፃደቁ የዘመኑ ምሁራኖች ናቸው ይህን የሚሰሩት ፡፡ ታዲያ ያወቁትና የተመራመሩት ምሁሮቻችን በእጅ አዙር ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ አሳቢ መስለው ለኢትዮጵያ ጠላቶች ነው የሚሰሩት? ያለፈው ታሪካችን አይነሳ ፤ ባለፈው የሰራነው ወንጀል ዛሬ ከምናራምደው ትግል ጋር በየትኛውም መልኩ አይገናኝም ፤ ዱባና ቅል ነው ይሉናል ፤ ታዲይ እነሱ ምኞታቸውን ለማሳካት ታሪካችን አይመርመር ስላሉ ብቻ እንዳሻቸው ይፈንጩ ብለን እንድንተዋቸው ይጠበቅብናል ማለት ነው?

እነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች ፍቅራቸውና ትሥሥራቸው ሀገርን ለማፈራረስና ለመገነጣጠል ከቆረጡት ጋር እንጂ ለኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ለዲሞክራሲ ከሚታገለው ጋር እንዳልሆነ እያስመሰከሩ በአንፃሩም እውነተኛ ታጋዩን ማዋከብና መምታት ሥራዬ ብለው የያዙት እንደሆነ ታሪካቸው መስክሮላቸዋል ። ያደረ አፋሽ በመሆን ወያኔ

እንደ ሽንኮራ አገዳ አላምጦ የተፋቸውን ሁሉ እያሳደዱ የሐገራችን አርነት አምጪዎች እንደሆኑ ይሰብኩናል ። ሥዩ አብረሃ ፤ ገብሩ አስራትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል ፤ ሰሞኑን ፓስተር ሆኛለሁ እያለ የሚያላግጠውንና እጁን በደም የታጠበውን ታምራት ላይኔንም ወያኔ አላምጦ ስለተፋላቸው መቼም ያደረ ማፈስ የለመዱ የዘመናችን ጉግ ማንጉጎች እሱንም አምጥተው በየአዳራሹ ህዝቡን እንደልማዳቸው ሰብስበው የኢትዮጵያ አለኝታ ይሄውላችሁ እንደሚሉን አትጠራጠሩ ።

በሌላው ወገን ደግሞ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ በቁርጠኝነት እየታገሉ ያሉትን ያለ ርህራሄ እየመቱ የ(OLF እና የ ONLF)የመሳሰሉትን የግንጠላ ቡድኖችን ሽኮኮ ብለው ያለ ሀፍረት የኢትዮጵያ አርነት አምጪኦች ናቸውና ተቀበሏቸው ይሉናል ፤

እነዚህ እራሳቸውን የወያኔ ተቃዋሚ ነን ብለው የሚጠሩ ነገር ግን በተግባር  ወያኔ አገዝ ድርጊቶችን እየፈጸሙ ያሉ ግለሰቦችና ቡድኖች እየተገበሩ ያለውን ድራማ በዝርዝር ሁሉንም ማስቀመጥ ባልችልም ዋና ዋና ናቸው ያልኳቸውን በመጠኑ ለመዳሰስ እሞክራለሁ ።

እንደሚታወቀው የነዚህ አስመሳይ ግለሰቦችና ቡድኖች ተጀምሮ እስከሚጨረስ አካሄዳቸውና አላማቸው በኢትዮጵያዊነት ካባ ጸረ ኢትዮጵያዊነትን ማራመድ እንደሆነ መተማመን የግድ ይላል ። ልክ ወዳጃቸው ጎጠኛው ወያኔ እንደሚያራምደው ፍቅራቸውና ትሥራቸው በዘርና በጎጥ ከተደራጁ ድርጅቶች እንጂ ከኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ጋር እንዳልሆነ እናውቃለን ። ኢትዮጵያዊውን ድርጅት መጠጋትም መንካትም አይፈልጉም ። ካላቸው አቋም ይፃረራልና ።

ከድርጊታቸውና ከታሪካቸው እንደተረዳነው የነዚህ አስመሳዮች ጥብቅ ወዳጅነትና ትስስር ጸረ ኢትዮጵያ ከሆኑት ከነ ሻቢያ ፤ ኦነግና  ኦብነግ ጋር እንደሆነ ያእባባይ ሚስጥር ነው ። እነሱም ከነዚህ ጸረ ኢትዮጵያ ድርጅቶች ጋር ማበራቸውና መተጋገዛቸውን የሚኮሩበት እንጂ የሚያፍሩበት እንዳልሆነ በድፍረትና በንቀት በተደጋጋሚ አሳውቀውናል ።

ኦነግና ኦብነግ ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ለመበታተን ታጥቀው የተነሱ የሻቢያ ቅፍቅፎች ብቻም ሳይሆኑ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊውን በቅኝ ገዢነት የሚወነጅሉ ፤ ኢትዮጵያዊነታቸውን የማያምን ፤ የማይቀበሉ ፤ በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች እንደ ግብጽ ፤ ሊቢያና የመሳሰሉት የአረብ መንግሥታት የሚደገፉ ፤ አልፎ ተርፎም ለሐገራችን ቀና ምኞት በሌላቸው በምእራባዊን መንግሥታት ታላቅ እንክብካቤ የሚደረግላቸው "ከፍሬው ገለባው" የሆኑ በፍርፋሪ አዳሪዎች መሆናቸውን እንደዛሬው ሳይጠነዙና ሳይገረዝዙ ገና በእንጭጭነታቸው ጀምሮ የምናውቀው ሆኖ ሳለ ፤ የኛ ተቃዋሚ ነን ባዮችና አራጋቢዎቻቸው እንደሚኩሏቸው መልከ ቀና ሳይሆኑ የህፃናትና የፍጥረት ማስፈራሪያ የሆኑ ጎዶች ናቸው ።

በመጀመሪያ ኦነግም ሆነ ኦብነግ በማያሻማ ቋንቋ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆኑና ከኢትዮጵያ ጋርም ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው ለአመታት እየነገሩን ሳለ በሌላ በኩል የኛ ተቃዋሚ ነን ባይ ነጋዴዎች ደግሞ ዘወትር ስለ ኦነግና ኦብነግ መሳደድና መሰቃየት ሲዘምሩ ይደመጣሉ ። ኦብነግንም ዛሬ የደረሰበት እንዲደርስ ያደረጉት እነዚሁ ተመፃዳቂና ንገሩን ባዮች እንደሆኑ ማወቅ ይኖርብናል ። ኦብነግ የሚባል ድርጅት እውቅና እንዲያገኝና ዛሬ የደረሰበት እንዲደርስ የረዳው የነዚሁ ቅጥረኞች የስራ ውጤት እንደሆነ ሁላችንም እናውቀዋለን ። (AFD) የሚባል በነዚሁ ነጭ አምላኪ ባንዳዎች ከተመሰረተ በኋላ ኦብነግ ሥሙ ገኖና መሳሪያም አንስቶ የማፈራረስ ትግሉን እንዲቀጥል አበረታቶታል ። ኦብነግ ከ  (AFD)መመስረት በፊት የት እንደነበረ የማይታወቅ ተራ የወንበዴዎች ጥርቅም እንደሆነ የማያውቅ አለ ብሎ መገመት ይቸግራል ። ታዲያ እነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች ጸረ ኢትዮጵያ የሆነን ድርጅት ማሳወቅና ማደራጀቱን ፤ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ድርጅቶችን መምታትና ማፈራረሱን ከወያኔ ባላነሰ የተካኑት ለመሆናቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም ።

ታዲያ እነዚህ እራሳቸውን ኢትዮጵያዊ አድርገው የማይመለከቱ እንዲያውም ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ምለውና ተገዝተው የተነሱ ድርቡሾችን መደገፍና የነሱን ልቅሶ አብረን ማልቀስ እንዳለብን ሊሰብኩን ሲዳዳቸው ዝም ብሎ መቀመጥ አግባብነት አይኖረውም ። እነዚህ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ያሉንንና ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ታጥቀው የዘመቱብንን ከጣሊያን ወራሪ ወይንም ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ከሚዘምት የግብጽ አሊያም መሰል የባእድ ጠላት

እንዴት ነው ለይተን ልናያቸው የምንችለው? በዚህ ሁኔታ ጣሊያንም ሆነ ድርቡሽ ቢመጣና የነሱ ሰራዊቶች ጥቃት ቢደርስባቸው ለነሱም ዘብ ጠበቃ ልንቆም ፤ ለድርቡሹም ለጣሊያኑም ልናለቅስ ይገባናል ማለት ይሆን? ኦነግና ኦብነግ ከውጪ ጠላት የሚለያቸውስ የትኛው ባህሪያቸው ነው? ይለቀስላቸው ብሎ ማላዘኑ ። እዚህ ላይ የራሳችንን አቋም ቆም ብለን ልንመረምር ይገባል ።

ኢትዮጵያዊው ለሚያደርገው የሀገር አድን ትንቅንቅ ከወያኔ በመለስ እንቅፋት የሆኑብንና ትግሉ አንድ ምዕራፍ ወደፊት እንዳይራመድ ከውጭ ኃይሎች በመለስ ፤ በግንጠላ ቡድኖችና በአድር ባይ አስመሳይ ታጋዮች በኢትዮጵያዊው ታጋይ ላይ በሚያደርሱት ጥቃት እንደሆነ ልናውቀው ይገባል ።

ልክ እንደ ኦነግና ኦብነግ እነዚህም በኢትዮጵያ ስም የሚምሉ ቡድኖች ዋና የገቢና የፍልስፍና ምንጫቸው የአረቡና የምእራቡ ክፍል መንግስታት እንደሆኑም ከማንም የተሰወረ አይደለም ።

እንደሚታወቀው የኦነግም ሆነ የኦብነግ አመራሮች በአሜሪካ ፤ በካናዳ ፤ በእንግሊዝና በመሳሰሉት የአውሮፓ ከተሞች ቪዛ ለማግኘትና ካንዱ አገር ወደ አንዱ አገር ለመመላለስ ምንም ችግር እንደሌለባቸው ይታወቃል ። እንደዚሁም አስመሳይ ታጋዮቹም እንደመሰሎቻቸው የተገንጣይ ቡድኖች የቪዛና የመዘዋወር ችግር የለባቸውም ። አይገጥማቸውምም ።

ነገር ግን እውነተኛውና ለኢትዮጵያ ለህዝቧ አሳቢ የሆነ ድርጅትም ይሁን ግለሰብ በነፃነት የመዘዋወር ፈቃድ ማግኘት አይችልም ። ለአብነት ያክል ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ከእስር ቤት ከተፈቱ በኋላ ወደ አሜሪካ ለህክምና ለመምጣት ገጥሟቸው የነበረውን የቪዛ ችግር  ማንሳቱ አይነተኛ ምስክር ነው ።  በአንፃሩ ግን የአፍራሹና የበታኙ ጋሻ ጃግሬዎች  ኢንጂነሩን የገጠማቸው ችግር አላጋጠማቸውም ። በዚህ ብቻም አላበቃም ኢንጂነሩ እንደምንም አሜሪካን ከገቡ በኋላ ህክምናቸውን ጨርሰው ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ በዝግጅት ላይ እንዳሉ እግረ መንገዳቸውን በካናዳና አውሮፓ የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ ለማነጋገር ወደ ካናዳና አውሮፓ ለመግባት የሚያስችል የቪዛ ፈቃድ ጠይቀው የተከለከሉ መሆናቸውን እናስታውሳለን ፤ ይህ ፈቃድ መከልከሉ ኢንጂነሩን ብቻ ሳይሆን ዶ/ር ታዬንም ይጨምራል ።

ታዲያ የምእራቡ ዓለም የወያኔን የግፍ አገዛዝ እንደሚደግፍ እናውቃለን ።  በጸረ ወያኔነት የቆሙ ግለሰቦችንም ይሁን ድርጅቶች መንገዳቸው ቀና እንዳይሆን ያልተቆጠበ ጥረት እንደሚያደርጉም እናውቃለን ፤ ስለሆነም በኢንጂነር ኃይሉም ሆነ በዶ/ር ታዬ ላይ የወሰዱት እርምጃ ለቆሙለትና ከሚደግፉት የወያኔ አገዛዝ ስሌት ስናየው አድራጎታቸው የሚደገፍ ባይሆንም እምነታቸውን የተከተለ መሆኑን ግን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መስታወት ሆኖ እናገኘዋለን ። ታዲያ የመግቢያና የመውጫ ፈቃድ የሚሰጣቸው እነማናቸው ብለን እራሳችንን ብንጠይቅ መልሱ የሚሆነው ወያኔ ፤ ሻቢያ ፤ ኦነግ ፤ ኦብነግና ግንቦት ሆነው እናገኛቸዋለን ማለት ነው ። እንግዲህ የሚያስብ አእምሮ ላለው ይሄ የሚነግረን ቢኖር ማንኛውም ጸረ ወያኔ ያልሆነ ፈቃድ ሲያገኝ ነገር ግን ጸረ ወያኔ ሆኖ የተገኘ ሁሉ እስፈላጊው ተጽዕኖ ይደረግበታል ማለት ነው ። ይህንን ለመረዳትና ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አይኖርብንም ።

እነዚህ አስመሳዮች ናቸው ዛሬ የኦነግና የኦብነግ እስረኞች እያሉ የሚያቅራሩብን ። ይሄ ለጩኸት የታደለው አፋቸው ግን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት በመታገላቸው የታሰሩትን ሞት ይመጣል እንጂ ስማቸው እንኳን እንዲነሳም አይፈልጉም ። እነ ጸጋዬ ገ/መድህን ፤ አበራሽ በርታና የመሳሰሉት የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ከጠላት ጎራ ተፈርጀው ስማቸውን ከማንሳት ይልቅ እየረጋገጡ ሲራመዱና ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ግለሰቦችን ስም ከፍ አድርገው ሲጮሁ መመልከት እጅግ አሳዛኝ ተግባር ሆኖ አግኝቼዋለሁ ።

ሰሞኑንም  ወ/ት ብርቱካንን ለማስፈታት በሚል ግርግር ይስተዋላል ። በጸረ ወያኔነት የታሰሩ ሁሉ በፖለቲካ አመለካከታቸው የተነሳ መታሰር እንደሌለባቸውና ለነጻነታቸውም መታገል ይገባል የሚል እምነቴ እንዳለ ሆኖ ። ነገር ግን የወይዘሪቷ ደጋፊዎችና የሷን አላማ የሚያራምዱ ሚዲያዎች አፍቃሪ ሻቢያ ፡ አፍቃሪ ወያኔ ፡ አፍቃሪ ኦነግና አፍቃሪ ኦብነግ በመሆናችው ብቻ እንደ ወይዘሪት ብርቱካን  የሆነች ኢትዮጵያዊት ታጋይ እህታችን ወ/ት መሶበወርቅ ቅጣው የወያኔ ሰለባ ሆና ወህኒ በወረደችበት ወቅት አንዳቸውም የሚዲያ ዘጋቢዎች ስለዚች ሀቀኛ

ታጋይ እህታችን የተነፈሱት ባለመኖሩ ሚዲያውም ሆነ ሚዲያው የሚያራግብላቸው በተቃዋሚ ስም የተሰለፉ አስመሳዮች የወያኔ ተቀጽላ እንጂ ሌላ ምንም እንዳልሆኑ ቁልጭ አድርጎ ማንነታቸውን አጋልጦታል ። እንደ አስመሳዮቹ ምኞትም ሳይሆን ግን ወ/ት መሶበወርቅ በቅርቡ ከወያኔ ወህኒ ቤት ወጥታ ዛሬ ከሚወዷትና ከምትወዳቸው ኢትዮጵያዊ ታጋዮች ጋር ተቀላቅላ መራራውንና እረጅሙን ትግል በቆራጥነት ተጋፍጣው ትገኛለች ። ታዲያ ማነው ለኢትዮጵያ የሚታገለው? ማነው ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚታገለው? መልሱ የተሰወረ ስላልሆነ ግንዛቤያችሁን ለናንተው እተወዋለሁ ።

ወያኔ በረቀቀ የአሰራር ችሎታው ከኛ እጅግ ልቆ በመምጠቁ ተፎካካሪ ሆኖ ለመቅረብ እያዳገተን የመጣ ይመስላል ፤ አሁንም ግለሰቦችን ያልሆኑትን እንደሆኑ አድርጎ የመቀበል አባዜያችንን የተረዳው ረቂቁ ወያኔ እስር ቤት ታስሮ መውጣት እራሱ ብቻውን የትግል መፈተኛና ማረጋገጫ አድርገን እንደምንወስድ ስለተረዳ አጅሬ ወያኔ የራሱን ሰዎች አግበስብሶ እያሰረ የኛ ጀግኖች እንደሆኑ አድርጎ ያቀርብልናል ። የኛም የወያኔ ተቀጥሎች ይህንን እያጋነኑና እያራገቡ የግለሰቦችን ተክለ ሰውነት መገንቢያና የውሸት ማንነት መፍጠሪያ ፋብሪካ አድርገውት እያየን ነው ። ነገም በረከት ስምዖን ወይንም ስዩም መስፍን ታስረው ከተፈቱ የኛ ጀግኖች መሆናቸው ነው መሰለኝ ? ያሳዝናልም ይገርማልም ።

ዛሬ በየዜና ማሰራጫው የሚመታው ከበሮ የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት ስለተጠራው ሰልፍ ነው ። የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት በሚደረገው ጥረት ላይ ምንም ተቃውሞ አይኖረኝም ። ነገር ግን ወገንታዊ ያልሆነና ሁሉንም ያካተተ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ ። የኛና የናንተ የሚለው ወያኔያዊ አሰራር እየታገልነው በመሆኑ በከንቱ ባንደክምና ብንታረም ለሁላችንም ይበጀናል ።

ሰልፉም ስውር ተልዕኮ አለው ብዬም አምናለሁ ። ይኸውም አንደኛ የኦነግና የብነግን ሰዎች ለማስፈታትና እንዲሁም እነዚህ የግንጠላ ቡድኖች እውቅናን እንዲያገኙ የተዘጋጀ በመሆኑ ፤ ሁለተኛ እውነተኛ ኢትዮጵያውያን ሆነው በፖለቲካ አመለካከተቸው የታሰሩትን ስለማያካትት ፤ ሶስተኛ ወያኔ የሚፈጥራቸውን ወያኔ ሰራሽ ጀግኖችን ተክለ ሰውነት ለመገንባት ሆን ተብሎ የተቀነባበረ በመሆኑ እቃወመዋለሁ ። ከፈረሱ በፊትም ጋሪውን በማስቀደሙ ትልቅ ጥያቄም አጭሮብኛል ።

ከፈረሱ በፊት ጋሪው ቀደመ ያልኩበት ምክንያትም በእውነት ሰላማዊ ሰልፍ መወጣት ከነበረበት 14 ሚሊዮን የሚሆነው ወገናችን ለረጅም ጊዜያት በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ፤ ህፃናት እንደ ቅጠል ሲረግፉ ለምን ሰልፉ አለተጠራም? ይህም ብቻ አይደለም ፤ ወያኔ የኢትዮጵያን ድንበር ቆርሶ ከሰሜን ጎንደር እስከ ጋምቤላ ያለውን ለም መሬታችንን አሻግሮ ለሱዳን መንግስት ሲሸጥ ለምን ሰልፍ አልተጠራም? በጎንደር ያለው ህዝብ ዳር ድንበሬን አላስደፍርም ብሎ ተነስቶ በሚዋጋበት ወቅት ወያኔ ከምስራቅ ድርቡሽ ከምዕራብ ሆነው እንደ ገና ዳቦ ከላይና ከታች እሳት ሲያነዱበት አስችሎን የተቀመጥን ፤ የሕአፓ የድርጅት አባሎች ለሃያ ዓመት በወያኔ እስር ቤት እየማቀቁ በህይወት መኖራቸውና አለመኖራቸው ባልታወቀበት ወቅት አንድም ቀን በነሱ ሁኔታ ከኢሕአፓና ከደጋፊዎቹ በስተቀር በተቀዳሚነት ማንም ድርጅት ሆነ ታዋቂ ነኝ የሚል ግለሰብ ለሰባዊ መብት እከራከራለሁ የሚል ጭምር ፤ የዲሞክራሲ ጥያቄውን እንተወውና እነዚህን የወያኔ ሰለባዎች አንስቶ በተቀዳሚነት ሰላማዊ ሰልፍ ሲጠራ ሰምቶም ሆነ አይተን አናውቅም ። እንዲያውም የነሱ ጥያቄ በሚነሳበት ሰዓት ወያኔን ተቃዋሚ ነን የሚሉት ሁሉ ለወያኔ ሃጢያት እነሱን ተጠያቂ ሲያደርጉ እንሰማለን ፤ አሁን ግን በቃን የምንልበት ደረጃ ላይ ስለደረስን ፤ አሁንም አንድ ሰው ታሰረብን በማለት ሰላማዊ ሰልፍ ሲጠራ የኢትዮጵያዊነት ይሉኝታ እንኳን ሳይዛችሁ ላለፈው ስራችሁ ሳትጸጸቱ ግለሰቦችን ለመገንባት የታቀደ ከመሆን ሌላ የሰባአዊ መብት ክርክር ፤ የዲሞክራሲ ፍትህና ርትዕ ጥያቄ መንፈስ እንደሌለው ፤ እውቅ መሆን አለበት ፡፡ የነ ደብተራውና የጓዶቹ ትግል ባምስትና በስድስት ዓመት የሚመዘን ሳይሆን ከአርባ ዓመት በላይ የተፈተነ ነው ፡፡ ይህንን የማያውቅ ፤ የማይቀበል ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ሰብአዊ መብት ክርክር አነሳለሁ የሚል ካለ የፖለቲካ መፃጉ ብቻ ነው ።

አሁንም ቢሆን ይህ ሁኔታ በቅጡ ካልተነገረና ካልታየ ጽሁፋችንም ይቀጥላል ፤ እኛም በጎራችን እናንተም በጎራችሁ ለማለትም እንገደዳለን ።

የነዚህን ከላይ የተጠቀሱ ክስተቶች ሚዛን ላይ አስቀምጦ ለተመለከተ በእውነት የትኛው ሚዛን ይደፋል ብሎ ለመገምገም አዳጋች አይሆንም ። በረሃብ ያለቀው ህዝባችን? ፤ ተቆርጦ ለድርቡሽ የተሸጠው ድንበራችን? ፤ ለዘመናት በወያኔ እስር ቤት ሲማቅቁ የቆዩት የፖለቲካ እስረኞች ? ወይስ አሁን የተጠራንበት የአንድ የግለሰብ ሰብአዊ መብት መገፈፍ? ፍርዱን ለአንባቢያን እተወዋለሁ ።

አሁን አሁንማ እነዚህ በጸረ ወያኔ ስም የተሰለፉ ቡድኖች ነገር ግን የወያኔ ካርቦን ኮፒዎች እድሜ ለኢትዮጵያ ጠላት የአረብ እና የምእራባውያን መንግስታት ኪሳቸው በዶላር ተወጥሮ የፈለግነውን ማድረግ እንችላለን በማለት ንቀትም እያሳዩ መምጣታቸው እየተስተዋለ ነው ።

በቅርቡ (ETV) የሚባል የቴሌቪዥን ጣቢያ አገር ቤት ልናስገባ ነው እያሉ ሲመጻደቁ ሰምተናል ። የሚገርመውና የሚያሳዝነው ግን በስደት ላይ የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ እንዳሳከሩት ሁሉ አገር ቤትም ገብተው ህዝቡን ለማወናበድ የሚያደርጉት ጽኑ ጥረት ነው ። ይህ የተጠቀሰው የቴሌቪዥን ጣቢያ እዚህ አሜሪካን ውስጥ 24 ሰዓት እየሰራ እንደሆነ ይታወቃል ። ባለንብረቶቹም እነማን እንደሆኑም ይታወቃል ። ነገር ግን እዚህ አሜሪካን ውስጥ ለ24 ሰዓት መስራት የሚችል የቴሌቪዥን ጣቢያ ማቋቋምና አልፎ ተርፎም ወደ አገር ቤት ለማስተላለፍ የሚዳዳ ተቋም ፤ የአረብ ወይንም የውጪ ኃይል በውስጡ የለም ለማለት እጅግ ያዳግታል ። ያም ከሆነ ደግሞ ግልጋሎቱ ለኢትዮጵያ እድገትና ብልጽግና ሳይሆን እንዴት ኢትዮጵያን ማፈራረስ እንደሚችሉ የሚተገብሩበት ትልቁ መሳሪያቸው እንደሆነ የምንክደው አይሆንም ።

አሜሪካን ውስጥ አንድ የቴሌቪዥን ሳይሆን የሬዲዮ ጣቢያ ለአንድ ሰዓት ስርጭት ለማዘጋጀት ከ$300.00 እስከ $400.00 የአሜሪካን ዶላር ይጠይቃል ፤ ያም ማለት ለ 24 ሰዓት ከ$7200.00 እስከ $9600.00 ሲጠይቅ በዚህ ሁኔታ አመቱን ሙሉ ለመቀጠል ከ $2.6 ሚሊዮን እስከ $3.5 ሚሊዮን ይጠይቃል ማለት ነው ። ይህ እንግዲህ የሬዲዮ ጣቢያ ወጪ ነው ። የሰራተኛውን ደሞዝና ሌሎች ሌሎች ወጪዎችን አይጨምርም ። የቴሌቪዥን ጣቢያ ደግሞ ከዚህ ወጪ እጅግ በጣም ከፍ ያለ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም ። በዚህ ሁኔታ የቴለቪዢን ጣቢያው በጣም ቢያንስ 10 ሰራተኞች ይኖሩታል ፤ የሚዲያ መገልገያ መሳሪያዎችንም መግዛት ይኖርበታል ፤ ምን ያክል ውድ እንደሆነ የማያውቅ ያለ አይመስለኝም ። በዚህ አገር ስሌት በጣም በትንሹ በአማካኝ ሰራተኞቹ በአመት የ $50000.00 ዶላር ደሞዝተኞች ቢሆኑ ግማሽ ሚሊዮን ዶላር ለደሞዝ ብቻ ይወጣል ማለት ነው ። እንግዲህ የቤት ኪራይ ፤ የመብራት የስልክ ፤ የነዳጅ ፤ የተሽከርካሪ መኪናዎችና የመሳስሉትንና ፤ ሌሎች ፤ ሌሎችንም ስንደማምር ወጪው እጅግ በጣም ብዙ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን ። ያንን ወጪ ለመሸፈን ደግሞ ያረጋሽ ምርጥ እንጀራና የቦቸራ የባህል ምግቤት ማስታወቂያ ወጪውን ይሸፍንላቸዋል ማለት በራስ መቀለድ ይሆናል ። ታዲያ ይህ ሁሉ ገንዘብ ከየት መጣ? የማንስ እጅ አለበት ብሎ መጠየቅ አግባብነት አለው ። ስለሆነም ማወቅና መጠየቅ ወንጀል ሳይሆን መብት መሆኑ መታወቅ አለበት ። በይሉኝታ አገራችን ስትፈርስ ቁጭ ብሎ መመልከት የጥፋቱ ተባባሪ ከመሆን የተለየ አይሆንም ። እናትህን ሊገድል የሚገሰግስን ገና አልገደላትምና እስኪገላት ታገስ ማለት በራስ ላይ ማሾፍ ይሆናልና ገና ለገና አፋቸውን ፈርቶ አገርን ያክል ክቡር ነገር ለቀን ጅቦች አሳልፈን መስጠት አይኖርብንምና አጥብቀን እናስብበት ።

የቴሌቪዥን ጣቢያውን አመሰራረትና በነማን እየተመራ ያለ እንደሆነና ቀዳሚ ተግባሩም ምን እንደሆነ ወደፊት በሰፊው የምናብራራበት ይሆናል ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!